# *የጋዜጠኛው ማስታዎሻ*

**በተስፋዬ ገብረአብ ተደርሶ በ2001 ዓ.ም. (በ2009 ዓ.እ) ኬፕ ታውን (ደቡብ አፍሪካ) የታተመ 31 ምዕራፍ ያለው ባለ 412 ገጽ መጽሐፍ**

**ጌታቸው ኃይሌ**

ይህ መጽሐፍ የትግሬ ወያኔዎች አገዛዝ ምን ዓይነት እንደሆነ ከውጪ የምንሰማውንና ያልሰማነውንም ሁሉ ፍርጥርጥ አድርጎ የሚናገር የዓይን ምስክር ነው። ደራሲው አቶ ተስፋዬ ገብረአብ ወያኔዎች ሥልጣን ሊይዙ ከአኮበኮቡበት ጊዜ ጀምሮ ሸሽቷቸው እስከሄደ ድረስ የጓዳ ሰዋቸው ሆኖ በጋዜጠኝነት ያገለገላቸው ሰው ነው። "አባይን በምን ይረቱ? በሚስቱ በእኅቱ" የሚባለውን ተረት በወያኔዎች ላይ አድርሶባቸዋል። ሚስትና እኅት ባላቸውን/ወንድማቸውን የማያስዋሹት፥ ውስጥ ዐዋቂዎች ስለሆኑ ነው እንጂ፥ ልዩ ፍጥረቶች ሆነው አይደለም። "ማን ይናገር? የነበር፤ ማን ያርዳ? የቀበር" የሚባለውም እውነቱን ከአሉ ባልታ ለመለየት ነው። አቶ ተስፋዬ ስለራሱ የሚናገረውን በጥርጣሬ ጆሮ ይሰሙት ይሆናል እንጂ፥ ስለወያኔዎች እውነቱን ከአሉ ባልታ ለይቶ ጽፎልናል፤ የጻፈውን የሚያጠራጥር ምክንያት አይታየኝም። ስለወያኔዎች ተንኮል የጻፈልን በሚሠሩት ሥራ በመሳተፍ በዓይኑ ያየውን በጆሮው የሰማውን ነው።

*የጋዜጠኛው ማስታዎሻ* የደረሰኝ አንዳንድ ነገሮችን ለመፈጸም በምቻኮልበት ጊዜ ሆኖ ሳለ፥ አንብቤው እስክጨርስ ሥራዬን ሁሉ እርግፍ አድርጌ ትቼው ነበር። የመጽሐፉ ምርኮኛ የነበርኩት በሁለት ምክንያት ነው፤ አንደኛ፥ ጠላትክን ዕወቅ ለሚለው ምክር ይጠቅማል፤ የእናት አገሬን የኢትዮጵያን ጠላቶች ከማውቀው ይበልጥ አሳውቆኛል። የትግሬ ወያኔዎች ለኢትዮጵያ አንድነት የሚታገለውን አገር ወዳድ ሁሉ፥ እንዴት አድርገው እንደሚያጠፉት ሳይደብቅ ይነግረናል፤ ግርግር አስነሥተው በጥይት ልብራሱን ይሉታል፤ ወዲያው ማን እንደገደለው ለማወቅ በሥራ ላይ እንዳይውል የታገደ ልል ትእዛዝ ይሰጣሉ። አስገዳዮቹ እነሱ መሆናቸው የሚታወቅባቸው ሲሆን ደግሞ፥ "ስምህን ለግድያ ከሚፈለጉ መካከል አይቸዋለሁና ነፍስህን አውጣ" የሚል መልእክት በሰው በኩል ይልኩለታል። ሰውየው ይኸን ሲሰማ፥ እንዳይታወቅ የገበሬ ልብስ ለብሶ በእግሩ ወደኬንያ ሲኳትን እነሱ ቁጭ ብለው ይስቃሉ። ፓትርያርክ መርቆርዮስን በሸኚ የላኳቸው በዚህ መልክ ነው፤ ጨርቃ ጨርቅ አልብሶ ይመራቸው የነበረው የወያኔ ነጭ ለባሽ ነበር። አቶ ተስፋዬ ሳይነግረን የቀሩ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፥ ስለ ምርጫ 97 የጻፈው አስገራሚ ቢሆንም፥ የፈለግሁትን ያህል አይደለም፤ ግን ብዙዎቹን ርእሰ ነገሮች የዘለላቸው የምናውቃቸው መስለውት ይሆናል።

ሁለተኛው ምክንያቴ የአጻጻፍ ዘዴው ነው። አቶ ተስፋዬ ገብረአብ የተዋጣለት የአማርኛ ደራሲ መሆኑን ማንም አስተዋይ አይክደውም። ራሱም እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "እነዚህን ሁሉ ገጾች የጻፍኩበት ቋንቋ የኔ አይደለምን? ይህን ቋንቋ ከኔ በላይ ማን ይራቀቅበታል?" በቋንቋው ከእሱ በላይ የሚራቀቅበት ማንም የለ ባልልም፥ አቶ ተስፋዬ እንደተራቀቀበት ለእኔ ግልጽ ነው።

ከአቶ ተስፋዬ ገብረአብ መጽሐፍ ብዙ ተምሬያለሁ። የዚች አጭር ድርሰት ዓላማዋ ያተረፍኩትን አዲስ ዕውቀት ለመዘርዘር ባይሆንም፥ ሁለቱን ላነሣቸው እፈልጋለሁ፤ አንደኛው ስለምርጫ 97 መጨናገፍ ነው። ስለዚህ ጉዳይ አቶ ተስፋዬ ከዚህ በታች ያለውን ጽፏል፤

> በመሰረቱ የኢህአዴግ ፖሊት ቢሮ አባላት በውጪ ሀገራት ባንክ በውጪ ምንዛሪ ያስቀመጡትን ገንዘብ መጠን ለማወቅ አስቸጋሪ ይሆናል። የኢህአዴግ ፖሊት ቢሮ አባላት የሚታመኑባቸው የእስያና የአውሮፓ ባንኮች የደምበኞቻቸውን መረጃዎች በቀላሉ የሚሰጡ አይሆኑም። ትንሳኤ ሬዲዮ (ያወጣባቸው) ትክክል የመሆን እድል እንዳለው የሚጠቁሙ ፍንጮችን ማንሳት ግን (የሚያስቸግር) አይሆንም።
>
> ምርጫ 97 ወደተቃዋሚዎቹ ባዘነበለ ጊዜ አብዛኞቹ የፖሊት ቢሮ አንጋፋዎች ሻንጣ ማሰር ጀምረው እንደነበር በቂ መረጃዎች አሉ። በስደት ሆኜ እንደሰማሁት

> ሹማምንቱ በግል ቤታቸውን ከማከራየት አንስተው ሚስትና ልጅን እስከማሸሽ ደርሰዋል፡፡
>
> በወቅቱ የመለስ ዜናዊ ባለቤት ልጆቿን ይዛ ወደለንደን አቅንታ ነበር፡፡ የተሰጠው ምክንያት "ልጆቹ ከጫጫታው ገለል ብለው እንዲቆዩ" የሚል ሆነ፡፡ . . .
>
> በምርጫ 97 ታሪካዊ እለት ዋዜማ የዶላር ምንዛሪ ዋጋ አሻቅቦ ነበር፡፡ ባለስልጣናቱ የሸሸጉትን ብር ሁሉ በጆንያ እየያዙ ዶላር ፍለጋ ተቅበዝብዘዋል፡፡ ጥቂት የማይባሉ ባለስልጣኖች ልጆቻቸውንና ሚስቶቻቸውን የምእራብ ሃገራትን ዜግነት ያስያዙ ሲሆን፥ የማይሰንፉባት ተግባራቸው ደግሞ ቪዛ ማደስን ነው፡፡
>
> የኢትዮጵያ ህግ ድርብ ዜግነትን አይፈቅድም፡፡ ይህ ህግ ግን ለባለስልጣናቱ አይሰራም፡፡

በዚያው ሰሞን ዶክተር አባ ጳውሎስም "ፓስፖርታችሁን ስታዘጋጁ እኔንም እንዳትረሱኝ" ብለው ባለሥልጣኖቹን ተማፅነው እንደነበረና እነቶኒ ብሌር ለመለስ ዜናዊ በአንድ የኢንተርናሽናል ድርጅት ውስጥ ሥራ ሊሰጡት ተዘጋጅተው እንደነበረም፥ ውስጥ ውስጡን ሲወራ ነበር፡፡ ከተስፋዬ መጽሐፍ ከአመጣሁት ከዚህ ጥቅስ ውስጥ ሁለት ነገር እረዳለሁ፤ አንደኛ፥ ኢትዮጵያን አሁን የሚገዙ ዜግነታቸው የሌላ ሀገር የሆነ ሰዎች ናቸው፡፡ ከሁሉም፥ ከሁሉም፥ ጠጉር የሚያስነጨው በምርጫ 97 ተቃዋሚዎቹ ድላቸውን በነዚህ ዜግነታቸው የሌላ ሀገር በሆነ ሰዎች ማስወሰዳቸው ነው፡፡ በምክንያቱ ብዙ ሰው ከሞተ በኋላ፥ በዚያው በመግፋት ፈንታ ሰዓት እላፊ ሲታወጅባቸው፥ በየቤታቸው ክትት ብለው፥ ለሞት ፍርድ በሚያደርስ ክስ ተከሰው እስር ቤት ገቡ፡፡ እኔም እንደእነሱ ፈሪ ስለሆንኩ፥ እዚያ ብሆን ኖሮ ምናልባት እንደዝምባብዌና እንደ ኬንያ ሕዝብ እንደምንም ጨክነን ሞተን ተሟሙተን ሕዝባችንን ነፃ እናውጣ ብዬ አልገፋፋም ነበር፡፡ ነፃነትን የሚያስገፍፍ ፍርሃት ነው፡፡

ሁለተኛው ዕውቀት ስለኢትዮሜዲያ (ethiomedia.com) ባለቤት ይከነክነኝ የነበረውን እንቆቅልሽ ገልጾልኛል፡፡ ከምርጫ 97 ቀደም ብሎ ጀምሮ ስለቅንጅት የሚነገረውን ዜና ለማወቅ ኢትዮሜዲያን በከፈትኩ ቊጥር ምንም አላገኝም ነበር፡፡ ለምሳሌ፥ በዚያው ሰሞን ቅንጅት ባደረገው በአንድ ታላቅ ሕዝባዊ የፖለቲካ ሰላማዊ ሰልፍና ትርኢት ላይ ኢትዮሜዲያ እንደመሪዎች አስመስሎ ያቀረበልን ተጋብዘው የመጡትን እንግዶች እንጂ፥ ሰልፉንና ትርኢቱን ያዘጋጁትን የቅንጅት መሪዎች አልነበረም፡፡ ቅንጅት ከተከፋፈለ በኋላ ደግሞ በኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል ስለሚመራው ፓርቲ ምንም ነገር አያመጣልንም ነበር፡፡ ምስጢሩን አሁን *የጋዜጠኛው ማስታወሻ* አወጣው፡፡ ምስጢሩን ለማፈን የተደረገው ሙከራም አልያዘም፤ ሙከራው ስለኢትዮሜዲያ ባለቤት የተጻፈውን ከመጽሐፉ ውስጥ ገንጥሎ ማውጣት ነበር፡፡ የሙከራው ፍሬ ጣፋጭ መሆኑ ቀርቶ መራር ሆነ፤ የገጾቹ መቀደድ ዜና ደጋፊዎቹን እስኪያሳፍር፥ የሚያምኑትን እስኪያሳዝን ድረስ ዓለሙን አዳረሰው፡፡

አቶ ተስፋዬ በዚህ በሾለ ብዕሩ ወያኔዎችን አገር ጥሎ እስከሄደ ድረስ እንደፈለጉት አገልግሏቸዋል፤ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ለጎሳዊነት ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ለማሳየት *የቡርቃ ዝምታ* የሚለውን መጽሐፍ ጽፎላቸዋል፡፡ በዚህ ቁጭት ያላቸው አንዳንድ ሰዎች፥ "እስከዛሬ የበደለው አንሶ አሁን ደግሞ ገንዘባችንን ሊያጋብስ ይኸን መጽሐፍ ጻፈ፤ የመጽሐፉ ቅጂ በኢንተርኔት ስለወጣ እየተቀባበልን እናንብበው እንጂ አንግዛው" ይላሉ፡፡ ቁጭቱ ይገባኛል፡፡ *የቡርቃ ዝምታ* የወያኔዎችን ጀግንነት ለመመስከርና የኦሮሞችን ልብ ለመማረክ የተጻፈ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ መሆኑን ማንም አይስተውም፡፡ ካስፈለገ ኦርሞዎችን ለማሞኘት የተፈጠረ አንድ ትርኢት ልጥቀስ፤ አንዲት ጸሐፊ ነኝ የምትል የኦሮሞ ተወላጅ ሴት ያንን በኋላ የገደሉትን ኀየሎም አርአያን እንዲህ ስትል ትጠይቀዋለች፤ "(በወያኔና በደርግ ፍልሚያ ጊዜ) አንድ ኦሮሞና አንድ የትግራይ ሰው ወድቀው ብታይ ቀድመህ የቱን ታነሣለህ?" ኦሮሞን ወዳጁ ኀየሎም ምንም ሳያወላውል፥ "ኦሮሞውን" የሚል መልስ ሰጣት፡፡ ሰውየውን ለማክሰርና ከተቃዋሚው ሰፈር ላለማስጠጋት የሚደረገው ሙከራ ግን አይገባኝም፡፡ አቶ ተስፋዬ እነዚህን ወንጀለኞች የተለያቸው ግብር አበራቸው መሆኑ አንገፍግፎት መሆኑን ብዙም አልጠራጠር፡፡

ከቀንዳሞቹ አንዱ ስለነበረ፥ ጥሎን ይሄድ ይሆናል ብለው አልጠረጠሩም፡፡ ቢጠረጥሩ ይኸን ሁሉ ምስጢር ይዞ የሚሄደውን ሰው በቦሌ አያሶጡትም ነበር፡፡ "እኛን ማጋለጥ ራሱን ማጋለጥ ስለሆነ አያደርገውም" ብለው ተሳሳቱ፡፡

ወያኔዎች አሁን ለማድረግ የሚችሉት፥ አንደኛ ማስፈራራት፥ ሁለተኛ መጽሐፉን ማፈን፥ ማስተባበል ወይም ሰውየውን ማክሰር ነው፡፡ ሁሉንም እየሞከሩ ነው፤ እሱም ጠባያቸውን ስለሚያውቀው፥ "የወያኔ ሰፊ ጆሮና እረጂም እጅ ይህን መፅሃፍ ከመሰራጨት መግታት ከቶውንም አይቻለውም" ሲል ገጽ 408 ላይ አስጠንቅቋቸዋል፡፡ እውነትም አልቻሉም፤ ወዳጅ ይሁን ጠላት ማን እንደጀመረው ባላውቅም መጽሐፉን ኢንተርኔት ለዓለም አዳርሶታል፡፡ ይህ የሆነው፥ ሌላው ቢቀር የመጽሐፉ ሽያጭ የማሳተሚያውን ዋጋ ከመለሰ በኋላ ቢሆን ደግ ነበር፤ ግን ድርጊቱ ወያኔዎች ሊያፍኑት አለመቻላቸውን አረጋግጦልናል፡፡

ኢትዮጵያውያንን ወዳስቆጣው ወደ*የቡርቃ ዝምታ* ልመለስና፥ መጽሐፉ ለወያኔ ከፋፍለህ ግዛው ፖለቲካቸው እንዲጠቅማቸው የተጻፈ በመሆኑ አልተገረምኩም፤ ጸሐፊው የወያኔ የፕሮፓጋንዳቸው መሪ ነበረ፡፡ መጽሐፉን ከማሳተሙ በፊት ረቂቁን ለአለቆቹ አሳይቷቸው እንደሚመቻቸው ለዋውጠው ሰጥተውታል፡፡ ለዘብ ቢያደርገው ደግ ነበር፤ የሱ ሥራ ይሁን ወይም አለቆቹ ለውጠውበት እንደሆን ባይገለጽም፥ የኢትዮጵያ ታሪክ በደነዝ ቢላዎ ሲታረድበት፥ አንዱ ቆሻሻና ሃይማኖተ ቢስ ሕዝብ የቀሩትን ንጹሓንና ሃይማኖተኞች ሕዝቦች በጭካኔ የጨፈጨፈ አድርጎ ያቀረበበትን *የቡርቃ ዝምታ* እስከመጨረሻው ላነበው የቻልኩት ኢትዮጵያችን ዛሬም እንደኀየሎም አርአያ ያሉ ጀግኖች የምታፈራ አገር መሆኗን ስላገኘሁበት ነው፡፡ እንዲህ ያለ ጭከና ያላቸው አማሮች እስከመፍጠር የደረሰው ግን፥ ምናልባት ሊቋቋመው ያልቻለው ተጽዕኖ ቢያመጡበት ይሆናል፡፡ ከሸዋ ውስጥ አንድ ጥሩ ሰው ቢፈጥር፥ አማራ ነው ብለን የምንሳሳት መስሎት፥ ወዲያው በረቀቀ ኢርቱዕ አጻጻፍ የሰውየውን ጉራጌነት ያረጋግጥልናል፡፡

ያዘንኩት አማራ በመሆኔ ለአማሮች ተቆጭቼ የሚመስላቸው ካሉ፥ ተሳስተዋል፤ ስሕተታቸው የራሳቸውን ጎሰኝነት ነው የሚገልጸው፡፡ ያዘንኩት እንዲህ ያሉ ኢትዮጵያውያን (ስተኛት "አቃታትና ሞተች፡፡ አልቻለችኝም፤ የገዛ ነጠላዋን አልብሻት ሄድኩ" የሚሉ ኢትዮጵያውያን) አሉ ተብሎ መጽጻፉ ነው፡፡ *የቡርቃ ዝምታ* እውነተኛ ታሪክ ከሆነ፥ ለኔ በውስጡ ያሉት ሁሉ ያጠፉትም የጀገኑትም ወገኖቼ ናቸው፤ በጀገኑት እኮራለሁ፤ በባለጉት አፍራለሁ፤ ስማቸውን በሚያጠፉት ጸሐፊዎች አዝናለሁ፡፡ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሰው፥ ውገናውን አማራነት፥ ኦሮሞነት፥ ትግሬነት፥ . . . ላይ ከመሠረተ፥ ከኢትዮጵያውያን ሊለይ የፈለገ የሰብአ ትካት (primitives) አባል ነው፡፡ ከአንድ ጎሳ መወለድ እንደ ሰው የቆዳ ቀለም ወይም ቁመት ባለበት የሚረሳ ነገር ሲሆን፥ የጎሰኝነት ስሜት ከተፈጠረ፥ ሀገር ስለሚጎዳ ከመሠረቱ ተነቅሎ ሊጣል የሚገባው ክሥተት ነው፡፡ አንድ ሰው ሀገረኝነትንና ጎሰኝነትን ይዞ መሄድ አይችልም፤ ሁለት ሃይማኖት እንደመያዝ ነው፡፡ ከሁለት አንዱን መምረጥ ይኖርበታል--ወይ ኢትዮጵያን ወይ ጎሳውን፡፡ ከአብሮ አደግና ከጎጥ ጋር መፋቀር ጎሰኝነት አይደለም፤ ጎሰኝነት በሀገር ጉዳይ ላይ ለአብሮ አደግና ለጎጥ ማዳላት ነው፡፡ አቶ ተስፋዬም ኢትዮጵያዊ ነኝ ስላለ ኢትዮጵያዊነትን ብቻ መምረጥ ይኖርበታል፤ ካልመረጠ፥ የሚጐዳው ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን፥ ለራሱም ቢሆን ወይ የኦሮሞ፥ ወይ የአማራ፥ ወይ የወላይታ፥ ወዘተ ጥገኛ መሆንን መምረጥ ሊኖርበት ነው፡፡ በአቶ ተስፋዬና ሰማንያ በመቶ በምንሆነው አማሮች መካከል ያለው ልዩነት እሱ የአያት የቅድም አያቶቹን ጎሳ ሲያስታውስ እኛ ዘመኑ ሩቅ ሆኖብን አለማስታወሳችን ነው፡፡

ግን መጽሐፉ ሰዎች አስቆጣ እንጂ፥ ወያኔዎቹን ምንም ያህል አልረዳቸውም፡፡ እንዲያውም የተጠሉትን የባሰ የሚያስጠላቸው መሆኑን አንዳንዶቹ ልብ እንዳሉት በአዲሱ መጽሐፉ ነግሮናል፡፡ ኦሮሞቹም ቢሆኑ፥ እነዚህ ሁሉን የሚረግጡና የሚንቁ ትምክሕተኛ ወያኔዎች ሄደው ዴሞክራሲ በሀገሪቱ ላይ ካልሰፈነ፥ የቡርቃ ወንዝ ዝምታ እንደማያከትም ያዩ ይመስለኛል፡፡ እኔን የገረመኝ ግን ሰውየው ስለመካ መዲናና ስለኦሮሞዎች ሙስሊምነት እያጎላ የጻፈው ልክ ታሪክ ጸሐፊው ሙሐመድ ሐሰን እንዳደረገው በኦሮሞች ስም ሙስሊሞችን ሊያነሣሣ እደሚችል ልብ አለማለቱ ብቻ ነው፡፡ ጨቋኝ ገዢ እንጂ ጨቋኝ ሕዝብ፥ ክፉ ሰው እንጂ ክፉ ሕዝብ፥ እንደሌለ በብዙው ስለተጻፈ፥ አልጨምርበትም፡፡

ታዲያ እንግዲህ፣ ዓላማውን ሊመታ ባልቻለ በቡርቃ ዝምታም ሆነ ወይም በሌላ ምክንያት፣ አቶ ተስፋዬን ለመጉዳት በወያኔ ተቃዋሚዎች በኩል የሚደረገው ሙከራ ስሕተት ይመስለኛል፤ እንዲያውም ይኸን ሙከራ የሚያደርጉት የወያኔ ደጋፊዎች ካልሆኑ፣ ባለማወቅ የወያኔ ደጋፊዎች ሆነዋል። አቶ ተስፋዬ ሀገር ጥሎ የወጣው እንደነ ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ፣ እንደነ አብርሃም በላይ፣ እንደነ አብርሃም ያየህ የወያኔ ተቃዋሚ እየመሰለ የወያኔ የውስጥ አገልጋይ ለመሆን እንዳልሆነ መጽሐፉን በዝግታ ላነበበ ሰው ግልጽ ነው። አቶ ተስፋዬ በዚህ መጽሐፍ ወያኔዎችን አያደሙ ማድማት አድምቷቸዋል። አውሬዎች ነበሩ፤ አሁን የቈሰሉ አውሬዎች አድርጓቸዋል። እናክስረው ከሚሉት መካከል፣ በዚህ ረገድ አንዳቸውም ይወዳደሩት አይመስለኝም። አንዳንዶቹማ ሰፈራቸውን ከተቃዋሚው ወገን ለማስመሰል ያህል ይንጫጫሉ እንጂ፣ ይኸን አስተዋጽኦ አደረጉ የሚባሉ አይደሉም።

አቶ ተስፋዬ በብዙ ዘዴና ወጪ ከወያኔ ለይቶ የሚያመጡት ሰው ሆኖ ሳለ አውቆ ሲመጣልን ቀጤማ ጎዝጉዘን በመቀበል ፈንታ፣ ካጋጠመን እንበቀለው ማለት የትልቅነትና የአርቆ አስተዋይነት ጠባይ አይደለም። ማጥቃት የጎበዝ ሥራ አቅምና ሥልጣን ባለው ላይ ሲሆን ነው። ያ የአቶ ተስፋዬ ዘመን አልፏል፤ የምንፈልገው በቀል ከሆነ፣ በቀል ወንጀልም ኀጢአትም ነው። በፖለቲካ ረገድማ፣ በቀል ጠላት ማፍራት እንደሆነ ከአፄ ምኒልክ ተምረናል። እንዲያውም፣ የወያኔን ወንጀለኞች ጥለው ለመሄድ የሚያስቡ ካሉ፣ አቶ ተስፋዬን ለነሱ መቀጣጫ ማድረግ አገርን መበደል ነው። እሱን ሳንቀበል ስንቀር፣ ሌሎች ወያኔዎችን ጥለው ለመሄድ የሚያስቡ፣ “ከነዚህም ከነዚያም እየተገላመጥን ከምንኖር ለራሳችን ስንል እዚሁ ከወንጀለኞቹ ጋር ሆነን እንረዳዳ” ነው የሚሉት። ሲ. አይ. ኤ. የደርግ ባለስልጣኖችን ያስከዳ የነበረው ጥሩ ሰው ለማግኘት ሳይሆን፣ ደርግን ለማድማት ነበር። የምሥራቅ በርሊን ወታደሮች ጠመንጃቸውን እየጣሉ ግምቡንና የሾሁን ሽቦ አጥር እየዘለሉ ወደ ምዕራብ በርሊን ሲመጡ፣ የምዕራብ በርሊን ሰዎች እያጨበጨቡ ይቀበሏቸው የነበረው የወታደሮቹ ጠመንጃ ደም እንዳፈሰሰ ሳይገምቱ ቀርተው ሳይሆን፣ የምሥራቁ የጭቆና ግዛት የሚያከትመው ደጋፊ ሲቀነስበት መሆኑን ስለተረዱ ነው። በ1933 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አርበኞች ከሱዳን በጎጃም በኩል እየገቡ የፋሺስት ኢጣልያ ባንዳዎችን እያስከዱ የጠላትን የጦር አቅም ማዳከማቸው የቅርብ ታሪካችን ነው።

አቶ ተስፋዬ በራሱ ኢትዮጵያዊነት ሙሉ እምነት አለው። በዚህ በሰላ ብዕሩ ጎሰኝነትን ኮንኖ ኢትዮጵያዊነትን አግንኖ እንዲጽፍ ልናበረታታው ይገባናል። ከልቡ ገንፍሎ በወጣው ጭቀኑን ኢትዮጵያዊነት ምክንያት፣ ፍላጎታችንን የራሱ ፍላጎት እንደሚያደርገው አልጠራጠርም፤ እሱ ከወዲያ እኛ ከወዲህ ተነሥተን ስንጓዝ አንድ ቦታ ላይ ተገናኝተናል። ጉዞውን የጀመረው እንደነ መለስ ዜናዊና እንደነ በረከት ሲሞን አብሯቸው አገር እንዳይቦጠቡጥ ሕሊናው የወቀሰው መሆኑን ከግምታችን ማውጣት የለብንም። የቡርቃ ዝምታው አኖሌ ዋቆ ኢትዮጵያዊነትን ትቶ ወደኦሮሞነት እንደተለወጠ፣ ተስፋዬም የጎሰኞችን ፖለቲካ ከማጠናከር ወጥቶ አገሬ ወደሚላት ወደ ኢትዮጵያ ስለተመለሰ፣ የጋራ አገራችንን የሚጠቅም መጽሐፍ ይጽፍልናል። ለኔ ወሳኙ፣ በእስረኝነቱ ጊዜ የጻፈው ሳይሆን፣ አሁን በነፃነት ባለበትና የእኛንም ስሜት በአነበበበት ጊዜ የሚጽፈው ነው። በዚያ ጊዜ፣ የቡርቃ ዝምታን የጻፈው “ምናልባትም፣ ኢትዮጵያን ለመግዛት የወደፊት ባለተረኞች ናቸው ብሎ የገመታቸውን ኦሮሞዎች ለመወዳጀት ይሆናል” የሚል አስተያየት ያለንን ወይ ያጸድቀው፣ ወይ ስሕተት መሆኑን ያሳየን፣ ወይ ይዘለው ይሆናል።

ስለዚህ በውጪ ሀገር ያሉ ከወያኔ ነፃ የሆኑ የተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ “የእንኳን ደኅና መጣህ” ጋዜጣዊ መግለጫ እንዲያወጡ፣ መጽሐፉን ከኢንተርኔት ያላገኙ እየገዙ እንዲያነቡት፣ ከኢንተርኔት ያገኙትም ዋጋውን እንዲከፍሉ አሳስባለሁ። እኔም ዋጋውን ለማን እንደምልክ ቢነገረኝ ወዲያው እልካለሁ። እስከዚያ ድረስም የአቶ ተስፋዬ ገብረአብ እናት የተቀበሩበት ቃጂማ ጊዮርጊስ ግብዝናው የአባቴ እንደነበረ ስጽፍለት ዜናውን የተቀበለው በአክብሮትና በደስታ ነው፤ መልሱ አብሮ ለመሥራትና ችሎታውን አገር ጥቅም ላይ ለማዋል በጎ ፈቃድ ያለው ለመሆኑ ከመጽሐፉ ያገኘሁትን ግምት አጽንቶልኛል።

በአለንበት አገር ቋንቋና አነጋገር፣ “Welcome, Ato Tesfaye GebreAb! Please challenge your colleagues, who are at present in the service of the enemy, to follow your footsteps.